


# የፖርትፎሊዮ ግምገማ

# ለአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ ለአፍሪካ (EUROPEAN UNION EMERGENCY TRUST FUND FOR AFRICA)

Funded by the European Union

**እ.ኤ.አ 2014 እና 2015 በሜዲትራንያን ባህር አካባቢ የስደተኞች ቁጥር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ጨምሯል። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ስደተኞች ሀገራቸው ውስጥ ባለው ውስን የኢኮኖሚ እድል ምክንያት ወይንም ደግሞ ከረጅም ጊዜ ግጭቶች ለመሸሽ ወደ አውሮፓ ህብረት መግባት የፈለጉ ናቸው።**

ስለዚህም የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት እና አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት እ.ኤ.አ. በህዳር 2015 ዓ.ም. በቫሌታ (ማልታ) በተካሄደው አለም አቀፍ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ስለስደት ዋነኛ መንስኤና ለተፈናቃዮች፣ በመፈናቀል ላይ ላሉት እና  ለመፈናቀል ተጋላጭ ለሆኑት መፍትሄ ለማበጀት ተወያይተዋል። ጉባኤው በአምስት ቅድሚያ የሚሳጣቸው ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች  እና አስራ ስድስት  ቅድሚያ በሚሰጣቸው የትኩረት ውጥኖች ዙሪያ የጋራ መግለጫ እና እቅድ ተጠናቋል።

በተጨማሪም በኖቬምበር 12, 2015 የሕገ-መንግስታዊ ስምምነት በ 25 የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት, ኖርዌይ, ስዊዘርላንድ እና የአውሮፓ ኮሚሽን የተፈረመ ሲሆን በአፍሪካ ውስጥ መደበኛ ያልሆነ ስደት እና መፈናቀል መንስኤዎችን ለመፍታት የአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ (EUTF for Africa) ከስትራቴጂ ጋር በይፋ ተቋቁሟል።   ይህ ስትራቴጂ በውስጡ ባሉት 4 ስትራቴጂክ አላማዎች፣ - የኢኮኖሚና የስራ እድልን ማሳደግ፣ የመቋቋም አቅምን ማጠናከር፣ የስደት አስተዳደርን ማሻሻል፣ እና የተሻቻለ አስተዳደር እና ግጭት መከላከል ላይ ያተኮረ ነው።

ይህ የአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ ፕሮግራም በሶስት አፍሪካ ክልሎች ማለትም በሰሜን አፍሪካ፣ ሳህል እና ቻድ ሀይቅ (SLC)፣ እና በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ላይ ተግባራዊ እየሆነ ነው። ፕሮግራሙ ከስትራቴጂካዊ ግቦቹ ጋር በተጣጣመ መልኩ አስቸኳይ የልማት እና የፀጥታ ፍላጎቶችን ለመቅረፍ ለአጋር ሀገራት እና ለፈጻሚ ኤጀንሲዎች እርዳታ ይሰጣል። ይህ በተለይ ለችግር የተጋለጡ እና የተገለሉ ወጣት ግለሰቦች ላይ ትኩረት በማድረግ አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማሳደግ እና የቅጥር ተነሳሽነትን ማሳደግን ይጨምራል።



# የአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ ለአፍሪካ ስትራቴጂያዊ አላማዎች

1. ከፍ ያለ የኢኮኖሚ እና የስራ እድሎች
2. ስደተኞችን እና የተፈናቀሉ ግለሰቦችን ጨምሮ በጣም ተጋላጭ በሆኑት ህዝቦች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ የማህበረሰቦችን የመቋቋም አቅም ማሳደግ።
3. በስደት መነሻ፣ መዳዳዣ እና መረሻ ሀገራት ውስጥ የስደት አስተዳደርን ማሻሻል
4. የተሻለ አስተዳደር እንዲኖር ማድረግ፣ ግጭትን መከላከል ወይም መቀነስ እና የግዳጅ መፈናቀል እና ህገ ወጥ ስደትን መቀነስ።

## EVALUATION SCOPE

እ.ኤ.አ. በ2021 ዓ.ም አላማውን ለዋና ባለድርሻ አካላት በ SLC እና HoA በስትራቴጂክ አላማ 1 በ EUTF ለለሚደገፉት ፕሮጀክቶች ውጤቶች እና ተፅዕኖዎች ተጨማሪ እውቀት እና መረጃ ለመስጠት አስቦ EUTF ተከታታይ የሆነ የካውንተርፋክቿል ግምገማዎች (CIEs) እና የፖርትፎሊዮ ግምገማዎች (PE) ጀምሯል።

ዋና ባለድርሻ አካላቶቹ የአውሮፓ ኮሚሽን፣ አስፈጻሚ አጋሮች፣ የአስተባባሪ ኮሚቴ አካል፣ ተሳታፊ መንግስታት፣ ድርጅቶች እና ሰፊውን ህዝብ ያካትታል።

ግምገማው ከ  ስትራቴጂክ አላማ 1 ጋር የተገናኙ የEUTF ፕሮጀክቶች ውጤታማነት እና ተፅዕኖ ላይ ቁልፍ የሆኑ ትምህርቶች፣ መደምደሚያዎች እና ምክሮች ላይ ግንዛቤን ይሰጣል።

በአጠቃላይ ግምገማው በ7 የተለያዩ ሀገራት፣ በድምሩ 9 ፕሮጀክቶችን (R1) እና 1 ፖርትፎሊዮ ግምገማ (R2) እንዲሁም በ8 ሀገራት ውስጥ 10 የጉዳይ ጥናት (Case studies) ፕሮጀክቶችን ያጠቃልላል።



**ሰንጠረዥ 1:** R1 ዲዛይን እና ዘዴዎች

| ፕሮግራም | አስፈፃሚ አጋር | ሀገር | የግምገማ ስልት (ስትራቴጂ) | የተቀላቃሉ ዘዴዎች ዲዛይን |
|---|---|---|---|---|
| STEDE | ሜርሲ ኮርፕስ | ኢትዮጵያ | RCT በተቀባይ ማህበረሰቦች እና IPWRA በስደተኞች ካምፕ ውስጥ | ኢክስፐሪመንታል እና ኳዚ ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን |
| TEKKI FII | GIZ | ጋምቢያ | IPWRA | ቀላል የጥራት አካል |
| GrEEn | UNCDF & SNV | ጋና | i) RCT ወይንም ማዛመጃ, ii) RDD ወይIPWRA, & iii) የፓናል መረጃ ትንተና | ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን & ተዛማጅ ኢምቤድድ ዲዛይን |
| INTEGRA | GIZ | ጊኒ | Clustered DiD with matching | ኳዚ ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን |
| INTEGRA | ITC | ጊኒ | RCT | ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን |
| PECOBAT | ILO | ሞሪታኒያ | Qualitative ዘዴ | የኳሊቴቲቭ ይዘት ትንተና |
| Promopêche | ILO | ሞሪታኒያ | Qualitative ዘዴ | የኳሊቴቲቭ ይዘት ትንተና |
| PARERBA | ENABEL | ሲኔጋል | IPWRA | ኳዚ ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን |
| RISE | GIZ | ኡጋንዳ | RCT | ኤክስፐሪመንታል ኢምቤድድ ዲዛይን |

**ሰንጠረዥ2:** R2 የጉዳይ ጥናቶች ግምገማ ዘዴዎች

| ፕሮግራም | ሀገር | አስፈፃሚ አጋር/አጋሮች | የግምገማ ስልት (ስትራቴጂ) |
|---|---|---|---|
| ABLI-G | ኬንያ | DRC, NRC, Intracen | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| LISEC Green Jobs | ኢትዮጵያ | PIN, IRC, Solidaridad | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| LISEC | ኢትዮጵያ | UNIDO | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| Jobs Creation and Trade Development | ደቡብ ሱዳን | ITC | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| JEEN | ኒጀር | SNV, Oxfam, DGD/CT, Partner for Innovation, UNCDF | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| DURAZINDER | ኒጀር | ENABEL | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| DESERT | ኒጀር | AICS, Terre Solidali, COOPI, CISP, COSPE | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| TUMMA | ቡርኪናፋሶ | ADA | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| I&P Acceleration au Sahel | ሲኔጋል | I&P (Terranga Capital) | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| I&P Acceleration au Sahel | አይቮሪኮስት | I&P (Comoe Capital) | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| SPRS-NU | ኡጋንዳ | ENABEL | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |
| SUPREME | ኡጋንዳ | World Vision, SNV, ZOA, RICE-West Nile | ውጤት መሰብሰብ እና የለውጥ ታሪኮች |

ግምገማው የፕሮግራሙ ስራን እና የስራ እድልን፣ ኑሮን እና መቋቋምን በማሳደግ ላይ ያለውን ተፅእኖ በተመለከተ ስድስት መሰረታዊ የግምገማ ጥያቄዎችን ለመፍታት ያለመ ነው።

በተጨማሪም፣ የታሰቡትን እና ያልታሰቡ ውጤቶችን፣ በጥናቱ ተሳታፊዎችና በተወሰኑ የተሳታፊ ክፍሎች መካከል ያለውን ልዩነት፣ ወጪ ቆጣቢነት እና የአውሮፓ ህብረት ለተነሳሽነቱ የሚያደርገውን አስተዋፅኦ ይገመግማል።

እነዚህ የግምገማ ጥያቄዎች በ SLC እና HoA  ክልሎች ውስጥ በስትራቴጂክ ዓላማ 1 (SO 1)  ስር ያሉትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመገምገም ይረዳሉ። ለምሳሌ ያህል በ SLC ክልሎች ውስጥ ያሉ የፕሮጀክት ውጥኖች ምን ያህል ለስደት ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው ክልሎች ውስጥ የኢኮኖሚ እና የስራ እድልን ለማሳደግ አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ እንድንገመግም ያስችሉናል። በተጨማሪም በክልሉ ውስጥ ካለው መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት ጋር በተያያዙ የስርዓቶች ለውጥ ላይ ግንዛቤዎችን ይሰጣሉ እንዲሁም የፕሮጀክት ተግባራት የአካባቢ ማህበረሰቦችን የመቋቋም አቅም እንዴት እንዳጠናከሩ እና እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ያስረዳሉ።

## የግምገማ ጥያቄዎች

**ጥያዌ 1፡** የ EUTF ፕሮግራሞች ለስራ እድል፣ ለስራ እድል ፈጠራና ሙያ ምን ያህል አስተዋፅኦ አድርገዋል?

**ጥያቄ 2፡** የ EUTF ፕሮግራም የተጠቃሚዎችን ኑሮ እና የመቋቋም አቅም በምን ያህል ቀይረዋል?


**ጥያቄ 3፡** የስራ እድልን ለመጨመር በጣም ወጪ ቆጣቢ የ EUTF ድጋፍ አማራጮች የትኞቹ ነበሩ?

**ጥያቄ 4፡** የ EUTF ፕሮግራሞች በሌሎች በታቀዱ እና ያልታቀዱ ውጤቶች ላይ ምን አስተዋፅኦ አድርገዋል? (ለምሳሌ ተንቃሳሽነት፣ ስደት፣ የስደት አላማዎች፣ የስራ ፖሊሲዎች እና ማሻሻዎች)

**ጥያቄ 5፡** የ EUTF ፕሮግራሞች ወጣቶችን፣ ሴቶችን፣ ስደተኞችን፣ ተፈናቃዮችን (ተፈናቃዮችን)፣ ስደተኞችን እና አስተናጋጅ ማህበረሰቦችን ጨምሮ የተለያዩ ተጋላጭ ቡድኖችን በእንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ ማካተት እና ማበረታታት የቻሉት በምን መንገዶች ነው?

**ጥያቄ 6፡** የEUTF ውጥኖች ከአባል ሀገራት፣ ገለልተኛ እና ልዩ የሁለትዮሽ ፕሮጀክቶች ጋር ሲነፃፀሩ ምን ያህል ውጤቶች ነበሩት?_ እንዲሁም የ EUTF ውጥኖች ከሌሎች አካባቢያዊ ፕሮጀችቶች ጋር ምን ያህል የተጣጣሙ ነበሩ?

**ምስል 1** ይህን የለውጥ ሂደት በጥናት ላይ ከዋሉት የግምገማ ጥያቄዎች ጋር ሲገናኝ ያሳያል



## የፖርትፎሊዮ ግምገማ አቀራረብ

የፖርትፎሊዮ ግምገማው በጥናቱ ላይ ስላለው አጠቃላይ እይታ ለመገንባት ዘዴዎችን ጥምር(አሃዛዊና አሃዛዊ ያልሆኑ) ዘዴዎችን በመተግበር ላይ ነው።

የፖርትፎሊዮ ግምገማው የፕሮጀክት ኋላፊዎችን ዳሰሳ፣ የክትትል እና የመማር ሲስተም ዳታ፣ ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለመጠይቆች፣ የዴስክ ጥናት ከውጤት አሰባሰብ ጋር፣ የለውጥ ታሪኮች፣ እና R3 ጋር ያለውን ትንተና ያዋሀዳል። (ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ 3 ይመልከቱ፡ R3 መሳርያዎች እና ሽፋን)

**ሰንጠረዝ 3:** R3 መሳርያዎች እና ሽፋን

| መሳርያ | ሽፋን | የእድገት ሁኔታ | ወጣ ያለ (የላቀ) |
|---|---|---|---|
| ፕሮጀክት ማናጀር ዳሰሳ | የሁሉም 84 ፖርትፎሊዮ ኮንትራቶች አጋር ፕሮጀክት ማናጀሮችን ማካተት | 31/84 | 53 |
| የዴስክ ግምገማ | የድርጊት ፊሽ፣ ROM ሪፖርቶች እና የግምገማ ሪፖርቶችን ጨምሮ ሁሉንም አስፈላጊ ዶክመንቶች | 209 የተገመገሙ ሪፖርቶች | እየተካሄደ ያለ |
| የውጤት መሰብሰብ | በኒጀር፣ ቡርኪናፋሶ፣ ሴኔጋል፣ አይቮሪ ኮስት፣ ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን እና ኬንያ ያሉ 10 ፕሮጀክቶች | 73 የተሰበሰበ ውጤት ከSLC እና 42 ከHoA | እየተካሄደ ያለ |
| የለውጥ ታሪኮች | በኒጀር፣ ቡርኪናፋሶ፣ ሴኔጋል፣ አይቮሪ ኮስት፣ ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን እና ኬንያ ያሉ 8 ፕሮጀችቶች | በኒጀር፣ ቡርኪናፋሲ፣ አይቮሪ ኮስት እና ሴኔጋል የመረጃ ስብሰባ ተጠናቋል | በኢትዮጵያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ኡጋንዳ እና ኬንያ የመረጃ መሰብሰብ እየተካሄደ ነው |
| የባለሙያዎች ቃለመጠይ1 (KII በመጠቀም) | በፖርትፎሊዮ ውስጥ የሚገኙ የአውሮፖ ህብረት ልዑካን እና የፕሮጀክት አስተዳዳሪዎች | 21 | 29 |
| R1 ተፅዕኖ ግምገማዎች | 9 በኢትዮጵያ፣ ጋምቢያ፣ ጋና፣ ጊኒ፣ ሞሪታኒያ፣ ሴኔጋል እና ኡጋንዳ ያሉ 9 ኮንትራቶች | ቢያንስ የመሀል መረጃ የሁሉም ሀገራት ተሰብስቧል<br><br>የመዝጊያ መረጃ ከኢትዮጵያ እና ሞሪታኒያ ተሰብስቧል | የጊኒ፣ ኡጋንዳ፣ ጋና እና ሴኔጋል የመዝግያ መረጃ |

# ፖርትፎሊዮ መገምገሚያ ዘዴዎች

**OUTCOME HARVESTING (OH)**

የተከናወኑ ተግባራትን ማስረጃ ለመሰብሰብ የሚደረግ የኳሊቴቲቭ መረጃ መሰብሰቢያ አካሄድ ነው፤ በተጨማሪም ፕሮግራሙ ለለውጥ አስተዋፅኦ እንዳበረከተና እና እንዴት እንደሆነ ለማወቅም ይሰራል። ውጤቱ ምን እንደቀየረ እና ማን ነው እንዲቀየር እንዳስቻለው እንዲሁም የት ላይ ለውጥ እንደመጣ በዝርዝር ያሳያል።

**የለውጥ ታሪኮች (SOC)**

ፕሮግራሙ ለተወሰኑ ውጤቶች ያለውን አስተዋፅኦ ለመመርመር እና ሪፖርት ለማድረግ የሚረዳ የኢንዳክቲቭ ጉዳይ ጥናት ዘዴ ነው። አንድ ፕሮጀክት በአንድ የተወሰነ ለውጥ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የቻለባቸውን ዘዴዎች እና መንገዶች ሪፖርት ያደርጋል።

**ቁልፍ የባለሙያዎች ቃለመጠይቆች (KIIS)**

የሚካሄዱት ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ሰፊ ልምድ እና እውቀት ካላቸው ግለሰቦች ጋር ነው።



## ትንታኔ እና አጠቃቀም

ከውጤት 1 (R1) የተገኙ ግንዛቤዎች በፖርትፎሊዮ ግምገማ ወቅት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ይጨምራሉ።

የሁለቱም ምንጮች መረጃ በአንድ ጊዜ እየተሰበሰበ ነው (ውጤት 1 እና ውጤት 2) እና ተሻጋሪ። ይህ ዘዴ (ትሪያንግሊንግ) በመረጃ ስብሰባ ወቅት የመረጃ አለመግባባቶችን (inconsistency) ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል፣ በዚህም መሰረት የEUTFን የአላማ 1 (objective 1)ን አፈጻጸምን በተመለከተ ማስረጃዎችን ለማቅረብ ይረዳል።

**ምስል 2፡** አጠቃላይ ግምገማን በአሃዛዊና አሃዛዊ ባልሆኑ ዘዴዎች ያሳያል




በአጠቃላይ እነዚህ ዘዴዎች በ EUTF የሚደገፉ ፕሮጀችቶች ኢኮኖሚያዊ እና የስራ እድል ተነሳሽነትን የማሳደግ አላማ እንዳላቸው እና በተጠቀሱት ክልሎች ውስጥ ስደትን ለመግታት ስላላቸው ተጽእኖ የበለጠ ሰፊ ግንዛቤን ይሰጣሉ። ግምገማው በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ማውጣትን ጠቃሚ ማስረጃዎችን እና ግንዛቤዎችን ለማቅረብ ይረዳል።

**አሃያዊ እና አሃያዊ ያልሆኑ ዘዴዎች ቀላቅሎ መጠቀም** የአንደን ፕሮግራም ለውጥ ከተለያዩ አመለካከቶች ለመመርመር እና በርካታ የምርምር ጥያቄዎችን ለመፍታት ጠቃሚ ናቸው። አሃዛዊ እና አሃዛዊ ያልሆኑ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኒኮችን በጥንቃቄ በማዋሃድ ተመራማሪዎች የፕሮጀክት ውጥኖች ከመፈፀማቸው በፊት፣ በነበሩበት እና በተከናወኑ ሂደቶች ላይ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

**ካውንተርፋክቹዋል ተፅዕኖ ግምገማ (CIE)** የአንድ ፕሮግራም በተጠቃሚዎች ላይ የሚኖረውን ተጨባጭ ውጤት ለማወቅ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ዘዴ ፕሮጀችቱ ተግባራዊ ባይሆን ኖሮ ምን ለውጥ ሊያመጣ ይችል ነበር የሚል ነው። ይህንን ደግሞ በቀጥታ ማየት ስለማንችል፣ ጥብቅ የኤክስፐሪመንታል እና ኳዚ ኤክስፐሪመንታል ዘዴዎች ካውንተርፋክቷሉን ለመገመት የአነፃፃሪ ቡድኖችን ይጠቀማሉ።

## የጊዜ መርሃግብሮች

በ4 ዓመት የግምገማ ጊዜ ውስጥ የሚከተሉት የፖርትፎሊዮ ግምገማ እና CIEs ይከናወናሉ

### 2021

የመነሻ ሪፖርትን ማጠናቀቅ እና በዲዛይን እና ግምገማ መንገድ ከEUTF ጋር መስማማት

### 2022

Q1 – ፕሮጀክት ማናጀር ዳሰሳ መጀመር

Q1 – የመጀመሪያ OH ዎርክሾፕ

Q3 – የመጀመሪያ KII ከፕሮጀክት ማናጀሮች እና EUDዎች

### 2023

Q1 – ሁለተኛ የOH ዎርክሾፕ

Q3 – ሁለተኛ ዙር KII ከፕሮጀክት ማናጀሮችና EUDዎች

### 2024

የመረጃ ትንተና እና ሶስትዮሽ ከCIEዎች ጋር፣ አጠቃላይ ትንተና እና የውጤት ስርጭት



Center for Evaluation and Development

EUTF for Africa

This publication was produced with the financial support of the European Union.
Its contents are the sole responsibility of the Center for Evaluation and Development (C4ED) and do not necessarily reflect the views of the European Union.
© 2023 Center for Evaluation and Development. All rights reserved. Licensed to the European Union under conditions.